 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

## መግቢያ

በባለፈው ጽሁፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ጥራዝ ሀ እና ለ የዳሰስን ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ከጥራዝ ለ የቀሩትን እና ሌሎቹን ጥራዞች በዝርዝር ለመዳደስ እንሞክራልን። በዛሬው ጽሁፍ የሕግ ተገዢነት መኮንን አስፈላጊነት እና ሚና፤ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈጻሚዎች በተለይም የገበያ ከፋች፣ ስፖንሰር አድራጊ ደላላ፣ የገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንዑስ ደላላዎች፤ የደንበኞች የካሳ ፈንድ እና ስለ ሁለቱ የሰነደ መአለ ንዋዮች ሜዝገባ ሰሌዳዎች እኔመለከታለን።

## የሕግ ተገዢነት መኮንንወሳኝ ሚናዎች

የመተዳደሪያ ደንቡ ጥራዝ ለ ስለአባልነት ደንቦች የተመለከተ ሲሆን የህግ ተገዢነት መኮንን ሚና በተመለከተ ትኩረት ተሰጥቶት የሚታይ ነው። የግብይት አባሉ የህግ ተገዢነት መኮንን ተፈጻሚነት ያላቸውን ደንቦች አተገባበር ምክር የመስጠት እና ጥሰቶችን በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። የህግ ተገዢነት መኮንኑ የሥራ መደብ ከሌላ ተቀራራቢነት ካለው የሥራ ኃላፊነት ጋር መጣመር የለበትም። ስለዚህ በግብይት አባሉ መዋቅር ውስጥ የህግ ተገዢነት መኮንን የስራ መደብ ከሌሎች የስራ መደቦች ጋር ተጣምሮ መመደብ የለበትም። በዚህ መደብ የሚሾሙ ሰዎች የሚሾሙበትም ሆነ የሚነሱበት አካሄድ የባለሥልጣኑን ይሁንታ የሚፈልግ ነው።

የሕግ ተገዢነት መኮንኑ ከሚያስፈልገው ነፃነት አንጻር በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የሚያደርግ ሲሆን ይህም መደብ የሚያገለግለውን ወሳኝ የድርጅቱን ጥቅም ጠባቂነት ተግባር ያንፀባርቃል። የግብይት አባላት ትርፋማ ለመሆን በሚያከናውኑት ሥራ እና ለተቆጣጣሪ አካላት እና በህግ ተገዢነት መካከል ከፍተኛ ግጭቶች በሚገጥሙበት ጊዜ የህግ ተገዢነት መኮንኑ ከሥነ ምግባር ጋር በተያያዘ እንደ መጀመሪያ ደረጃ የአደጋ ስጋት መከላከያ ሆኖ ያገለግላል።

የሕግ ተገዢነት መኮንኑ በኢንቨስትመንትና የካፒታል ገበያ አስተዳደር ውስጥ የሚፈጠሩ የቁጥጥር ሥርዓቶችን ለውጦችን በተከታታይ እየተከታተለ ለግብይት አባሉ፣ ለተሿሚ እንደራሴዎቹ እና ለሌሎች ስራተኞች እንዲሰራጭ እን እንዲያውቁት ያደርጋል። ይህ በደንቦች፣ መመሪያዎችና ፖሊሲዎች ላይ የሚኖሩ ለውጦችን በመከታተል ለአባላትና ለሰራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ ሂደት፣ ሥጋትን ለመከላከል የሚያስችሉ የቁጥጥር ፕሮግራሞችን ማበልፀግ፣ ስልጠናና ትምህርት ማዘጋጀት፣ የተፈጠሩ ጥሰቶችን ማስተካከል እና የግብይት አባሉ በሕጎችና በውስጥ መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ያካትታል። በአጠቃላይ የሕግ ተገዢነት መኮንኑ የውስጥ አሰራሮቹን ከተለዋዋጭ ህጎች አንጻር በመቃኘት እና እንዲስተካከል በማድረግ የሕግ ተገዢነት ሥርዓቱ እንዲሰራ ያደርጋል።

## የሰነደሙዓለ ንዋዮችግብይት ፈጻሚዎች

በመተዳደሪያ ደንቡ የትርጓሜ ክፍል እንደተገለጸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ማለት እንደ አግባብነቱ የደንበኞችን መመሪያ/ትእዛዝ የማስፈጸም እና/ወይም ስፖንሰር ለሚያደርጉት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የራሳቸውን ገንዘብ በመጠቀም ግብይቶችን የመፈፀም ኃላፊነት ያለው ግለሰብ ነው። የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈጻሚ በጥራዝ ለ ከተመለከቱት የተገበያይ አባላት አይነት ውስጥ አንደኛው ነው። በዚህ ክፍል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት የሚፈጽሙ አባላት ማሟላት ያለባቸውን መስፈርቶችን ያስቀምጣል። እነዚህም ከባለሥልጣኑ ፈቃዶችን ማግኘት፣ የገበያውን ስልጠና ፕሮግራሞችን ማጠናቀቅ እና የተገቢንት እና ብቁነት ደረጃዎችን ማሟላት አለባቸው። በገበያው የሚያዘው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈጻሚዎች መዝገብ ለመገበያየት የተፈቀደለት ሰው ማን እንደሆነ ለማወቅ ግልጽነት ይፈጥራል። በገበያው እስካልተፈቀደ ድረስ አንድ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ ሊቀጠር እና ሊሰራ የሚችለው ለአንድ (1) የግብይት አባል ብቻ ነው።

በባለስልጣኑ ለግብይት አባሉ በሚሰጠው የአገልግሎት ፈቃድ መሰረት የግብይት አባሉ የሚቀጥራቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚዎች መደቦች ሶስት አይነት ሲሆኑ እነዚህም የደንበኞችን ግብይት የሚያስተዳድር የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ (ዎች)፣ የግብይት አባሉን የራስ የሆነ ግብይት የሚያስተዳድር የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ፈፃሚ (ዎች)፣ እና ፈቃድ የተሰጠው ገበያ ከፋች ተገበያይ ናቸው።

## የገበያ ከፋቾች

በጥራዝ ለ ስር ከተካተቱት የግብይት አባላት አይነቶች ሌላኛው የገበያ ከፋች ነው። በአዋጁ እንደተመለከተው ገበያ ከፋች ማለት ባለሥልጣኑ ተግባራዊ በሚያደርገው የቁጥጥር ስርዓት መሠረት ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አቅርቦት እና ፍላጎት እንዲኖር የሚያደርግ ሰው ነው። የገበያ ከፋች በገበያው ቶሎ የመሸጥ እና የመግዛት ሁኔታን ለመፍጠር ቀጣይነት ያለው ፍላጎት በማሳየት ተከታታይ የመግዣ እና የመሸጫ ዋጋ የሚሰጥ ልዩ አባል ነው። የብቁነት መስፈርቶቹ ተገቢ የሆነ ካፒታል፣ ብቃት ያለው ሠራተኛ፣ በቂ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት እና ተገቢ የቁጥጥር ፕሮግራሞችን ይፈልጋሉ።

በገበያ ከፋቾች ላይ የተጣሉ ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች ከጠበቅ ያሉ ናቸው። አንደኛው ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው ገበያ ከፋቹ ገበያው በሚወስነው ከፍተኛው እና ዝቅተኛው የዋጋ ልዩነት መጠን ውስጥ እና ገበያው በየጊዜው ከሚወስነው ዝቅተኛ መጠን ባላነሰ ሁኔታ በግብይት ስርዓቱ ላይ የዋጋ ማቅረቢያ እና የዋጋ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

ገበያ ከፋቹ ለመግዛት የሚያቀርባቸው የዋጋ ማቅረቢያ እና ለመሸጥ የሚያቀርባቸው የዋጋ ጥያቄ ማቅረቢያ ከገበያው ጋር በገባው ውል በተመለከተው መሰረት ዝቅተኛ መጠን እና ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። ገበያ ከፋቹ እነዚህን የዋጋ ማቅረቢያ እና የዋጋ ጥያቄ ማቅረቢያ ክዋኔዎች ከዘጠና ቀናት በላይ ማቆየት መቻል አለበት። ይህን ማድረግ አለመቻል የገበያ ከፋቹን መብትን የሚያስነሳ ውጤት ያስከትላል። እነዚህ መስፈርቶች የገበያ ከፋቾች ተጓዳኝ ግዴታዎችን ሳይወጡ ጥቅሞች ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ የሚያደርጉ አስገዳጅ ሁኔታዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

## ስፖንሰርአድራጊ ደላላ፣ የገበያ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ ዲጂታል ንዑስ ደላላዎች

ዲጂታል ንዑስ ደላላ ማለት፣ በዲጂታል መንገድ የካፒታል ገበያ አገልግሎቶችን ለደንበኞች የሚያቀርብ ንዑስ ደላላ ነው። እነዚህ ደላላዎች በቀጥታ ከገበየው ጋር የሚሰሩ አይደሉም፤ ይልቁንም ከተፈቀደለት ስፖንሰር አድራጊ የኢንቨስትመንት ባንክ፣ ይሰነደ ሙአለ ንዋይ አከናዋኝ ወይም ደላላ በኩል የሚገናኙ ናቸው። በተለምዶ ስራቸው ሰነዶችን የመግዛት እና የመሸጥ፣ የሰነዶች ዋጋዎችን በዲጂታል ቻናሎች (ሞባይል መተግበሪያ፣ በድህረ ገጽ መድረክ ወዘተ) ለደንበኞች ማቅረብ ነው።

ዲጂታል ንዑስ ደላላ ማለት፣ በዲጂታል መንገድ የካፒታል ገበያ አገልግሎቶችን ለደንበኞች የሚያቀርብ ንዑስ ደላላ ነው። እነዚህ ደላላዎች በቀጥታ ከገበየው ጋር የሚሰሩ አይደሉም፤ ይልቁንም ከተፈቀደለት ስፖንሰር አድራጊ የኢንቨስትመንት ባንክ፣ ይሰነደ ሙአለ ንዋይ አከናዋኝ ወይም ደላላ በኩል የሚገናኙ ናቸው። በተለምዶ ስራቸው ሰነዶችን የመግዛት እና የመሸጥ፣ የሰነዶች ዋጋዎችን በዲጂታል ቻናሎች (ሞባይል መተግበሪያ፣ በድህረ ገጽ መድረክ ወዘተ) ለደንበኞች ማቅረብ ነው።

አንድ የግብይት አባል በዲጂታል ንዑስ ደላላ በኩል ለራሱ መለያ መያዝ፣ እንደ ደንበኛ ሆኖ መሥራት ወይም ለራሱ መለያ ግብይት ማድረግ የተከለከለ ነው። እንደ ስፖንሰር አድራጊ አካል እውቅና ማግኘትን በተመለከተ የግብይት አባሉ ከዲጂታል ንዑስ ደላላ ጋር ግብይቶችን ከመጀመሩ ቢያንስ አስር የስራ ቀናት በፊት በተወሰነው ፎርማት በመጠቀም ለገበያው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት። ይህ ማስታወቂያ ለዲጂታል ንዑስ ደላላ እና ለግብይት አባሉ የባለሥልጣኑ የአገልግሎት ፈቃዶች ቅጂዎች፣ በግብይት አባሉ የተፈረመ የዋስትና እና የካሳ ሰነድ እና በገበያው የሚጠየቁ ሌሎች ማንኛውም መረጃ አብሮ መቅረብ አለበት። አንዴ እውቅና ከተሰጣቸው በኋላ፣ የስፖንሰር አድራጊው ደላላ፣ አከናዋኝ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ የዲጂታል ንዑስ ደላላዎች ሚና ደንበኞች በገበያው ላይ ሰነዶችን እንዲገዙ እና እንዲሸጡ ዲጂታል ቻናሎችን በማቅረብ ብቻ የተገደበ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

## የደንበኞችየካሳ ፈንድ

ሌላው የመተዳደሪያ ደንቡ ጥራዝ ለ ክፍል 3 (ምዕራፍ 11-12) የተካተተው የደንበኞች የካሳ ፈንድ ነው። ይህም በደንቡ ውስጥ ካሉት በጣም ጉልህ ከሆኑ የኢንቨስተር ጥበቃ ዘዴዎች አንዱን ያቋቁማል። ይህ ፈንድ ከግብይት አባላት ተወካዮች፣ ከገበያው፣ ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት፣ ከባለሥልጣኑ እና ከተመዘገቡ ባለአክሲዮኖች ማህበራት ተወካዮች በሚወጣጡ በገለልተኛ ቦርድ የሚተዳደር ሲሆን ዋናኛ አላማው በግብይት አባላት ስህተቶች እና ውድቀቶች ምክንያት ኢንቨስተሮች ላይ ለሚደርስ ኪሳራ የካሳ ክፍያ መፈጸም ነው። በዚህ ክፍል ምዕራፍ 11-12 ውስጥ ያሉት የካሳ ድንጋጌዎች የይገባኛል ጥያቄዎችን ማረጋገጫ፣ የክፍያ ውሳኔዎችን እና ንዑስ ክፍያን የሚመለከቱ ሂደቶችን ያስቀምጣሉ። ከፍተኛው የካሳ መጠን የሚወሰነው በፈንዱ ቦርድ ሲሆን፣ ኢንቨስተሩ ለኪሳራው ኃላፊነት ከወሰደ ወይም ሌሎች ምክንያቶች ካሉ፣ የይገባኛል ጥያቄዎች ወዲያውኑ ካልቀረቡ ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ።

ለካሳ ፈንድ መመስረት ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉ መነሻዎች አንዱን ማየት ይቻላል። ኢንቨስተሩ ሰነድ እንዲገዛለት የመረጠው ደላላ ቢከስር ወይም ጉዳት ቢያደርስበት፣ ግዛልኝ ካለበት ገንዘብ በላይ ቢገዛለት፣ ሽጥልኝ ካለበት ገንዘብ በታች ቢሸጥለት፣ ግዛልኝ ካለው የሰነድ አይነት ውጪ ቢገዛለት፣ እንደነዚህ እና መሰል አይነት ኪሳራ ቢያስከትል ምን ይሆናል? በደላላው በኩል የሚነግዱ ኢንቨስተሮች በደላላው ጉድለት ጉዳት ወይም ኪሳራ እንዳይደርስባቸው በመከላከል እንዲሁም ኪሳራ ሲደርስባቸው ያንን የመካስ ስራ ለመስራት እንዲህ አይነቱን የደንበኞች የካሳ ፈንድ ማቋቋም ሰፊ የገበያ ተሳትፎን ያበረታታል። ኢንቨስተሮች በሚመርጡት የግብይት አባላቸው ከመተማመናቸው እና ተስፋ ከማድረግ ባለፈ ኪሳራ ቢደርስ የሚካሱበት ስርዓት መኖሩን ያረጋግጣል።

እዚህ ጋር ይሄ የደንበኞች ካሳ ፈንድ በአዋጁ ከተመለከተው አጠቃላይ የኢንቨስተር ካሳ ፈንድ የሚለይ መሆኑ ልብ ይለዋል። በዚህ ከላይ የተገለጸው የደንበኞች ካሳ ፈንድ በገበያው የተመዘገቡ የግብይት አባላት በደንበኞች ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት የሚክሱበት ሆኖ የሚቋቋመው በአባላት ማዋጮ ሲሆን በባለስልጣኑ ደረጃ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚቋቋመው የካሳ ፈንድ እንደ አጠቃላይ በገበያው የሚገበያዩ የግብይት አባላትን ጨምሮ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና በገበያው በራሱ የውል ግዴታን ካለመወጣት በኢንቨስተሮች ላይ የሚደርስ ጉዳትን ወይም ኪሳራን ለመካስ ያለመ ነው።

## ጥራዝ ሐ፡ የምዝገባ ደንቦች—ሰነዶችን ወደ ተማከለ ገበያ ማምጣት

ጥራዝ ሐ የሚጀምረው አጠቃላይ መርሆዎችን በመከተል ነው። የመተዳደሪያ ደንቡ ጥራዝ ሐ በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የምዝገባ መስፈርቶችን እንዲያወጣ፣ ቀጣይ ግዴታዎችን እንዲያስተዳድር፣ መተዳደሪያ ደንቦችን እንዲገመግም እና እንዲያሻሽል፣ ምዝገባዎችን እንዲያግድ ወይም እንዲሰርዝ ለገበያው ሥልጣን ይሰጣል። ይህ ስልጣን ገበያው በተደጋጋሚ የሕግ ማሻሻያዎችን ማድረግ እና ማውጣት ሳያስፈልገው ለተለዋዋጭ የገበያ ሁኔታዎች እና ለሚከሰቱ ችግሮች ምላሽ መስጠት እንደሚችል ያረጋግጣል።

## ሁለት አይነት የሰነደሙ አለ ንዋይ የምዝገባ ሰሌዳ መዋቅር

ከጥራዝ ሐ ጉልህ ከሆኑት ባህሪያት አንዱ እና ዋነኛው ለሰነዶች ግብይት ሁለት የተለያዩ አይነት የምዝገባ ሰሌዳዎችን ማቋቋሙ ነው። እነሱም የዋና ገበያ ምዝገባ ሰሌዳ እና የአዳጊ ገበያ ምዝገባ ሰሌዳ ይባላሉ። ይህ ባለሁለት የምዝገባ ሰሌዳ መዋቅር በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ላይ ያሉ ኩባንያዎች የተለያዩ ባህሪያት እንዳላቸው ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደየእድገት ደረጃቸው የተለያዩ የምዝገባ መስፈርቶችን በማጥናት የተዘጋጀ ነው። ለሁሉም ኩባንያዎች ተመሳሳይ መስፈርቶችን መተግበር ተስፋ ሰጪ እድገት ላይ ያሉ ኩባንያዎችን የሚያገል በመሆኑ፣ ነባር ከፍተኛ እድገት ላይ የደረሱትን ኩባንያዎች ገና በማደግ ላይ ካሉት ጋር አንድ ላይ ማድረግ ደግሞ የምዝገባ መስፈርቶቹን ደካማ የሚያደርግ በመሆኑ ሁሉንም እንደየእድገት ደረጃቸው ታይተው በሁለት ተከፍለው የምዝገባ መስፈርቶች ተዘጋጅቶላቸዋል።

የገበያው ዋናው ገበያ የምዝገባ ሰሌዳ (ምዕራፍ 5) ትላልቅ እና የበለጠ የተደራጁ ኩባንያዎችን ኢላማ ያደርጋል። በዋና ገበያ የምዝገባ ሰሌዳ ላይ ኩባንያውን አስመዝግቦ ሰነዶቹን ለመገበያየት ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የሥራ አፈጻጸም ሪከርድ፣

 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

ከሶስቱ አመታት ቢያንስ በአንዱ ከግብር በኋላ ትርፍ ያስመዘገበ መሆን፤ ሲመዘገብ ቢያንስ አምስት መቶ ሚሊዮን ማርኬት ካፒታላይዜሽን (የገበያ ዋጋ ግምት ይለው ሰነደ ሙአለ ንዋይ) በባለአክሲዮኖች የተያዙ መሆን አለባቸው (ይህ ማለት የአንዱ አክሲዮን ዋጋ ሲባዛ በአጠቃላይ የኩባንያው አክሲዮኖች ብዛት ቢያንስ ከ500 ሚሊዮን ብር)፣ የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበባቸው ሰነደ ሙአለ ንዋዮች መካከል ቢያንስ አስራ አምስት በመቶ (15%) የአውጭው አክሲዮኖች ቢያንስ በ300 የህዝብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ወይም እንደ የውክልና ሻጭ የሚያገለግሉ የኢንቨስትመንት ባንክ ወይም በተቋማዊ ኢንቨስተር መያዝ አለበት። ይሁን እንጂ የ15% መስፈርት ጋር በተያያዘ ቢያንስ ሁለት ቢሊዮን ብር (2,000,000,000) ካፒታላይዜሽን ያለው አውጪ አሥር በመቶ (10%) ብቻ ለግብይት የቀረበ አክሲዮን እንዲኖረው ሊፈቀድለት ይችላል። እነዚህ እና ሌሎች በደንቡ የተመለከቱ ተጨማሪ መስፈርቶች የሚያሟሉ በዋናው ገበያ የምዝገባ ሰሌዳ የሚመዘገቡ እና የሚገበያዩ ይሆናል።

ይህ የተለየ አካሄድ ለገበያ ልማት ወሳኝ ነው። የዕድገት ቦርድ ከሌለ ብዙ ተስፋ ሰጪ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች የሕዝብ ኢንቨስትመንት እንዲደርስ የሚጠይቅ ደረጃ እስኪያገኙ ድረስ የሕዝብ ገበያዎችን ማግኘት አይችሉም።
በቀጣይ ሳምንት እትም ከኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ጥራዝ ሐ የቀሩትን እና ጥራዝ መ እና ሠን በጥልቀት የምንዳስስ ይሆናል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT